# እኔ ሙስሊም ነኝ

አዘጋጅ
ሙሐመድ አሽረፍ ሶላሕ

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

﴿ وَمَن يَبۡتَغِ غَيۡرَ ٱلۡإِسۡلَٰمِ دِينٗا فَلَن يُقۡبَلَ مِنۡهُ وَهُوَ فِي
ٱلۡأٓخِرَةِ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ﴾ [آل عمران : ٨٥]

ከእስልምና ሌላ ሃይማኖትን የሚከተል ሰው
ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም እርሱም
በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው



**Copyright, distribution and translation are reserved for every Muslim**


| | |
|---|---|
| **Legal Deposit No.** | **22274 / 2008** |
| **International Serial** | **977-6157-64-5** |


**For charitable distribution call:**
**0020101459613**

**For suggestions e-mail:**
**anamuslim@windowslive.com**

**WWW.Iam-Muslim.com**

# 1 - በአላህ ማመን

## እኔ ሙስሊም ነኝ .. .. .. .. ..

* አጋሪ የሌለውና ከሱ ሌላ ጌታ በሌለው ብቸኛው አላህ አምናለሁ ፤ አልወለደም አልተወለደም ለሱም ምንም አምሳያ የለውም ::

* ሰማያትንና ምድርን የፈጠረና የነሱም ባለቤት ነው ፤ ሩቁንም ሆነ ቅርቡን ያውቃል ፤ የማይሞት ሕያውና የማይተኛ ዘወትር ንቁ ነው ::

*ለሱም ደጋግ ስሞችና ተላላቅ ባህሪዎች አሉት ፤ ከነሱም ዘጠና ዘጠኝ ስሞቹ የሚካተቱ ሲሆኑ በመወሰን ያወቃቸውና በነሱም የጸለየ ጀነትን ይገባል ::

* ከነሱም የአንድነት ባህሪው ይካተታል ፤ ጥራት ይገባውና ታላቁ አላህ አንድ ፤ አሃድ ፤ ብቸኛ የሁሉም መጠጊያና የንግስና ባለቤት ነው







* የግርማ ባህሪ ፤ እሱ ጥበበኛ ፤ ውስጥ አዋቂው ፤ ቅኑ ፤ ሕያውነቱ የተረጋገጠው ፤ ፊት ያለው ፤ ኋለም ቀሪው ፤ ግልጹ ፤ ስወሩ ፤ የዓለሙ ወራሽ ፤ ለዘላም ኗሪው ፤ ተብቃቂው ፤ ቅዱሱ ፤ መስካሪው ፤ ቅርቡ ፤ ዳንኛው ፤ ፍትሃዊው ፤ የሰማያትና የምድር ብርሃኑ ፤ የግርማና የመከበር ባለቤቱ ጌታ ነው ::

* የታላቅነት ባህሪ ፤ እሱ አሸናፊው ፤ ከቡሩ ፤ ታለቁ ፤ የላቀው ፤ ሃያሉ ፤ ብርቱው ፤ ጠንካራው ፤ አምበርካኪው ፤ ቻዩ ፤ ባለችሎታው ፤ ረጂው ፤ እጅግ የበላዩ ፤ ከሁሉ በላዩ ጌታ ነው ::

* የችሎታ ባህሪ ፤ እሱ አዋቂው ፤ ሰሚው ፤ ተመልካቹ ፤ ሕያው ፤

ጨባጩ ፤ ለቃቂው ፤ ዝቅ አድራጊው ፤ ከፍ አድራጊው ፤ አክባሪው ፤ አዋራጁ ፤ ሰጪው ፤ ከልካዩ ፤ ጠቃሚው ፤ ጎጂው ፤ ሕያው አድራጊው ፤ ገዳዩ ፤ ወደፊት አስቀዳሚው ፤ ወደኋላ አስቀሪው ጌታ ነው ::

* የመፍጠር ባህሪ ፤ እሱ ፈጣሪው ፤ አስገኚው ፤ ቅርጽ አሳማሪው ፤ አግኚው ፤ አድስን ሁሉ ፈጣሪው ፤ መፍጠርን ጀማሪው ፤ መፍጠርን መላሹ ፤ ቀስቃሹ ፤ ሰብሳቢው ፤ አጅጉን ለጋሱ ፤ በሰፊው ከፋቹ ፤ ሲሳይን በገፍ ሰጪው ፤ አብቃቂው ፤ የሁሉን መጠን አዋቂው ፤ ባሮቹን ጠባቂው ፤ ጠባቂው ፤ ተጠባባቂው ፤ ሰማያትና ምድርን ያለብጤ ፈጣሪው ጌታ ነው ::

* የእዝነት ባህሪ ፤ እሱ እጅግ ርህሩሁ ፤ አጅግ አዛኙ ፤ በሰፊው አዛኙ ፤ ያለወሰን ሰጪው ፤ ወዳዱ ፤ ደጉ ፤ በሰፊው መሀሪው ፤ ይቅር ባዩ ፤ በጂጉ ጸጸትን ተቀባዩ ፤ የሰላም ባለቤቱ ፤ ጸጥታን ሰጪው ፤ ርህሩሁ ፤ አመስጋኙ ፤ ቸሩ ፤ ተድላ ሰጪው ፤ ለጋሱ ፤ አጋዡ ፤ ጸሎት ተቀባዩ ፤ ችሮታው ሰፊው ፤ ታገሹ ፤ ቅኑን መንገድ መሪው ፤ ለቅጣት የማይቸኩለው ፤ ዕውቀተ ረቂቁ ፤ መመኪያው ፤ የጭንቅ ደራሹ ፤ እግዛና የሚጠየቀው ፤ ጸጸት ተቀባዩ ጌታ ነው ::

* ለሰው ልጅ ስፍር ቁጥር የሌለው ጸጋ ሰጥቷል ፤ ማንኛውም ባሪያ የሚደሰትበት ጸጋ ከአላህ ብቻ







ያገኘው እንጂ አይደለም :: አሱ ያ የፈጠረው ፤ ሕያው የደረገው ፤ ለሱም መስሚያና ማያ ያደረገለት ፤ ያከበረው ፤ ሲሳይን የሰጠውና ውለታን የዋለለት ጌታ ነው ::

* በመሆኑም በማንኛውም ባሪያ ላይ በአምልኮት አላህን በቸኛ አድረጎ የማምለክ ግዴታ አለበት :: - አሱም ተእዛዙን ለመፈጸም መገዛትና የከለከለውን ነገር መራቅ ነው :: ምክኒያቱም ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባው ማነም የለምና ::

* እንደዚሁም አላህ በመታዘዘም ሆነ በማመፅ የባሪያውን ሁኔታዎች ያውቃል ::

ስለዚህ ባሪያው ልቡን ፤ ጥራት ይገባውና በታላቁ አላህ አክብሮት ፤ ታላቅነትና ፍቅር የመሙላትና ታላቁ አላህ ሲፈጽማቸው ይመለከተዋልና በኃጠ ያቶቹ አፍሮ ከነሱ የመራቅ ግዴታ አለበት ::

* እንዲሁም ጥራትና ክብር ይገባውና ወደ ፈጣሪው ውዴታ የሚያቃርቡ መልካም ሥራዎችን በምስጢር የማከናወንና ከነሱም ከኢሕሳን -አላህን እንደምናየው ሁነን መገዛት- ደረጃ እስከሚደርስ

* ስለሆነም ማንኛውም መሲልም በመቃብር ላይ ሊጸልይ ፤ የተቀበረው ሰው ማንም ይሁን ማን ባለመቃብርን መጠጠየቅ ፤ አይፈቀድለትም ፤ እሱ አይሰማውምና ፤ እንዴት

ጸሎቱን ይቀበል ወይስ ይጠቅመዋል ? አላህ ብቻ ነው የሚጠቅመውና የሚጎዳው ፤ በመሆኑም በሙስሊም ላይ ይህን ነገር ነብዩ - ሰ.ዐ.ወ - ከልክለዋልና መቃብሮች ላይ መስጊድ ያለመስራት ግዴታ አለበት ።

* እንዲሁም አንድ ባሪያ የሱን ደካማነትና - ክብርና ግርማ ይገባውና - የአላህን ኃይል ፤ የሱን ፈላጊነትና - ክብርና ግርማ ይገባውና - የአላህን ተብቃቂነት ፤ የእሱን አለማወቅና - ክብርና ግርማ ይገባውና - የአላህን ዕውቀት ፤ የሱን ወራዳነትና - ክብርና ግርማ ይገባውና - የአላህን ክብር የማጤን ግደታ አለበት ።

* ክብር ለአላህ ለመልእክተኛውና ለምእምናን መሆኑን ሊያውቅ ይገባል



እኔ ሙስሊም ነኝ

የመጨማመር ግዴታ ይኖርበታል ። ምክኒያቱም እምነት በመገዛት ይጨምራል እንዲሁም በውንጀልም ይቀንሳልና ።

* ለስሜት ፤ ለፍላጎትና ለፈሊጥ ነገሮች መገዛትን ትቶ የነብዩን ትእዛዛት በመከተል ለአላህ ብቻ መገዛት ይኖርበታል ። በሥራውም የዚህችን ዓለም ተድላ ሳይሆን የአላህን ምንዳ ብቻ የሚፈልግ ሊሆን ይገባል ።

* አንደዚሁም አላህ ለሰው ልጅ እናት ለልጇ ካለት እዝነት የበለጠ አዛኝ ነው ፤ አዝነቱም ሁሉን ነገር ሸፍኗል ። በመሆኑም በባሪያው ላይ በዚህችም ዓለም ሆነ በመጭዋ ዓለም ፍላጎቱ እሱን የመለመንና የመማጸን ፤ በአንጻሩም ሌላን ያለመጠየቅ ግዴታ አለበት ።

* ይህውም ፤ ካአላህ በስተቀር ሙሉ ችሎታ ያለው የለምና ነው ፤ ከአላህ ሌላን መጸለይ ፋይዳ የለውም ፤ ምስጢርና ሹክሹክታን አላህ እንጂ አይሰማም ፤ ፍርድና ውሳኔም በአላህ እጅ እንጂ አይደለም ፤ ጸሎትን የመቀበል ችሎታ በአላህ እጅ ብቻ ነው ።

* እንዲሁም ከነዚያ ፣ በአላህ ላይ እንጂ ከማይመኩ ፣ ከአላህ እንጂ እግዛናን ከማይጠይቁ ፣ በአላህ እንጂ ከማይይበቁ ፣ አላህን እንጂ ደረስልን ከማይሉ ፣ አላህን እንጂ ከማይፈሩ ፣ አላህን እንጂ ከማይከጅሉ ፣ አላህን እንጂ ከማይጸልዩ ፣ ለአላህ እንጂ ከማያርዱ ፣ ለአላህ አንጂ ስለት ከማይገቡ ፣ በአላህ እንጂ ከማይምሉ ፣ ክታብም ሆን ሕርዝ ከማያደርጉ ፣ ካህናት ፣ ኮከብ ቆጣሪዎችና ድግምተኞችን ከማያምኑ እንዲሁም ወደነሱ ከማይሄዱ ምእምናን የመመደብ ግዴታ አለበት ::

* ከነዚያ መጥፎ ገድ ከማይፈሩት ፣ ወደ ገሀነም እንዳይንሸራተቱ ከምላሳቸው ዳጥ ከሚጠነቀቁ ምእምናን ሊሆን ይገባል :: እነሱም የአላህ ፈቃድና የእገሌ ፈቃድ ከሆነ ፣ አላህና አንተ ባትኖሩ ኖሮ ፣ በአላህና በአንተ ተመካሁ አይሉም :: ነገር ግን በአላህ ብቻ እመካለሁ ፣ የአላህ ፈቃድ ከዚያም የእገሌ ፈቃድ ከሆነ ፣ ይላሉ :: ምክኒያቱም ቀደምቱ ቃላት ከአላህና ከባሮቹ መካከል እኩልነትን ይጠቁማሉና ::





እነሱም ከትንሹ ማጋራት ይመደባሉ :: እኛ በአላህ የማመን ግዴታ እንዳለብን ሁሉ ፣ ጣዖታትን የመካድ ግዴታም አለብን ::

* የጣዖታት ቁንጮ ደግሞ ዳቢሎስ ነው :: እንዲሁም ከአላህ ሌላ በፈቃዱ አምልኮት የተደረገለት ሁሉ ጣዖት ነው :: አላህ የተፈቀደ ያደረገውን ነገር የሚያርም ወይም እርም ያደረገውን የሚፈቅድ ህግ የደነገገ ሰው ከነዚያ ጣዖታት ይመደባል ::

* ወደዚህ ነገር ጥሪ ያደረገ ወይም በሱ ያዘዘ ወይም በሱ የፈረደ እንደዚሁ ጣኦት ነው :: ምክኒያቱም ከመስማትና ከመታዘዝ በማመጽ የፍጡርን ወሰን ተላልፏልና ::

* አላህ የሰዎች በቸኛ ፈጣሪ በመሆኑ የሚበጃቸውን ያውቃል ፣ እናም ያለሱ ማንም ህግን ሊደነግግላቸው ከቶ አይችልም ::

# 2 - በመልአክት ማመን

ታለቁ አላህ ከብርሃን በፈጠራቸው መልአክት አምናለሁ :: እሱም ሁለት ሁልት ፤ ሦስት ሦስት ፤ አራት አራት ክንፍ ያደረገላቸው ሲሆን ፤ አይበሉም ፤ አይጠጡም ፤ አይተኙም ፤ ሚስትም አያገቡም :: በሥራዎችና ተልእኮዎች አዟቸዋል ፤ አነሱም በትክክል የፈፀሚቸዋል ::

* መልአክት ዘወትር ተገዢዎች ናቸው :: አይደክሙም ፤ አያምጹም ፤ ከበላያቸው ጌታቸውን ይፈራሉ ፤ ከነሱም አላህ ምድርና ሰማያትን ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ እስከትንሳኤ ቀን ድረስ በግንባራቸው ተደፍተው የሚገዙና ያን እለት ቀጥ ሲሉ ጥራት ይገባህና የሚገባህን ያህል አልተገዛንህም የሚሉ ይገኛሉ ::

* እነሱ የአላህ ባሪያዎች እንጂ ሴት ልጆች ወይም የሱ አጋሮች አይደሉም :: እነሱ በትንሳኤ ቀን - በአለህ ፈቃድ - ለምእምናን ይማልዳሉ ::





* ከነሱም ጠባቂዎች ይካተታሉ ፤ እነሱም እነዚያ ባሮችን ከመጥፎ ነገር የሚጠብቁት ናቸው ::

* ከነሱም የተከበሩት መዝጋቢዎች ናቸው ፤ እነሱም እነዚያ ደግም ሆነ መጥፎ - መልካም ሥራና መጥፎ ሥራ - የባሮችን ሥራዎች የሚመዘግቡት ናቸው ::

* ከነሱም አሞጋሾች ይካተታሉ ፤ እነሱም እነዚያ ያለ መድከም ቀንና ሌሊት እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ የሚያሞግሱት ናቸው ::

* ከነሱም መካከል ጎብኚዎች ይገኛሉ ፤ እነሱም እነዚያ በጸሎት ፤ በቅዱስ ቁርአን ንባብና በትምህርት ቦታዎች የሚገኙት ናቸው ::

* ከነሱም የእጅግ ርህሩሁን ዙፋን ተሸካሚዎች ይካተታሉ ፤ ቁጥራቸው ስምንት ሲሆን ከአላህ ፍጥረታት እጅግ ተላላቆቹ ናቸው ፤ አንድ በራሪ ካንደኛቸው ጆሮ ጫፍ ተነስቶ ካንገቱ ለመድረስ የአምስት መቶ ዓመት በረራ ይፈጅበታል ::

* ከነሱም የሞት መልኣክ ይካተታል ፤ አሱም ያ በአላህ ትእዛዝ የባሮችን ነፍስ የሚያወጣው ሲሆን ለሱም ተባባሪዎች አሉት ።

* ከነሱም መካከል እስራፊል ይገኛል ፤ እሱም ከትንሳኤ ቀን በፊት በቀንዱ በሚነፋበት ጊዜ ፍጥረታት በሙሉ ይሞታሉ ፤ ከዚያም እንደገና ሲነፋው ተነስተው የሚያዩ ይሆናሉ ።

* ከነሱም መካከል ሚካኢል ይገኛል ፤ አሱም የእንጥብጣቤ -ዝናብ- ኃላፊ ነው ።

* ከነሱም ሪድዋን ይካተታል ፤ እሱም የጀነት አሳላፊ ሲሆን በጀነት ምእምናን ለማገልገል ሽርጉድ የሚሉ ተባባሪዎች አሉት ።

* ከነሱም መካከል ማሊክ ይገኛል ፤ አሱም የገሀነም ኃላፊ ሲሆን በርካታ - አዛዦቻቸው ዐሥራ ዘጠኝ የሆኑ - ከሃዲዎችን በገሀነም የሚያሰቃዩበት የብረት መዶሻ የያዙ ተባባሪዎች አሉት - ከዚህ ዓይነቱ ስቃይ በአላህ እንጠበቃለን - ።







* ከመልአክትም ግንባር ቀደም የሚሆነው ጂብሪል ነው ፤አሱም ወደ መልእክተኞችና ነብያት ትንቢት የማድረስ ኃላፊነት የተሰጠው ነው ።

* ነብዩ -ሰ.ዐ.ወ - ከግዙፍነቱ አድማሶችን ሸፍኖና ስድስት መቶ ክንፎች ያሉት ሁኖ በእውነተኛ ገፅታው አይተውታል ። አሱ ያ የሎጥን መንደር በክንፉ ጫፍ ሲወጋት ወደ ሰማይ ጫፍ አርጋ ተገልብጣ የተደፋችውና የላይዋን ወደታች ያደረጋት ነው ።

* ከነሱም ሌሎች በዙዎች ይገኛሉ - የጌታህን ሰራዊት አሱ ራሱ እንጂ ማነም አያውቀውም - ።

﴿وَمَا يَعۡلَمُ جُنُودَ رَبِّكَ إِلَّا هُوَۚ﴾ [المدثر:٣١]

* መልእክት አላህ የሚወዳቸውን ምእምናን ይወዳሉ ፤ ለነሱም ይጸልያሉ ፤ ከአላህ ዘንድም ምህረትን ይጠይቁላቸዋል ።

* መልኣክት በዚህ ሁሉ ኃይላቸው ከምእምናን ጎን ተሰልፈው ይዋጋሉ ።

# 3 - በመጽሓፍት ማመን

* አላህ ወደ መልእክተኞች ባወረዳቸው መጽሓፍት አምናለሁ ፤ እነሱም - በመሰረቱ ካለህ የወረዱት - የሱን ህግና ሃይማኖት እንዲያስተምሩ ወደነሱ በትንቢት ያወረደው ያለህ ቃል በመሆናቸውም አምናለሁ ። ከነዚህ መጽሓፍት ተላላቆቹ የሚከተሉት ናቸው ።

* በመልእክተኞችን ሙሐመድ - ሰ.ዐ.ወ - ላይ የወረደው ቅዱስ ቁርኣን

* በሳቸው ላይ ሰላም ይውረድና በዒሳ ላይ የወረደው ኢንጂል ።

* በሳቸው ላይ ሰላም ይውረድና በሙሳ ላይ የወረደው ተውራት ።

* በሳቸው ላይ ሰላም ይውረድና በዳውድ ላይ የወረደው ዘቡር ።







* በሳቸው ላይ ሰለም ይውረድና በኢብራሂም ላይ የወረዱት ጽሑፎች

* ከነዚህ መጽሓፍት ቅዱስ ቁርኣን ከመውረዱ በፊት መሰረታቸው ተለዋውጧል ።

* ቅዱስ ቁርኣን በነዚህ መጽሓፈት የበላይነት ያለው ሲሆን የህግጋቶቻቸውና የደንቦቻቸው የበላዩ ነው ። እንዲሁም ከሱ ደንቦቹ ጋር የሚፃረሩትን እንደወረደ የሰረዘ መጽሓፍ ነው ።

* አላህ በትንሳኤ ቀን በቅዱስ ቁርኣን ደምብ የተሠሩ ሥራዎችን እንጂ አይቀበልም ። ይህን ማለትም በሙሐመድ - ሰ.ዐ.ወ - ላይ ቁርኣን ከወረደ በኋላ ከዚያ በፊት በነበሩት መጽሓፍት ደምብ የተሠሩ ሥራዎችን አይቀበልም ማለት ነው ።

* ቁርኣን ታምራታዊ የሆነው የአላህ ቃል ነው ፤ የተቀደሰ ሲሆን ከፊቱም ሆነ ከኋላው ከንቱ ነገር አይጠጋውም ። በሱ የተናገረ እውነተኛ ፤ በሱ የፈረደ ፍትሃዊ ይሆናል ። እንዲሁም በሱ የሠራ ቅኑን መንገድ የተመራ ፤ እሱን አጥብቆ የያዘ

አሸናፊና ስኬታም ፤ እሱን የተወ ደግሞ ከጠፊዎች ይሆናል ::

* የቁርኣን ሰዎች እሱ የመረጣቸው የአላህ ሰዎች ናቸው ፤ ከሰዎች በላጬ ቁርኣንን የተማረና ያስተማረው ነው ፤ ምክኒያቱም በትንሳኤ ቀን ላነበበው ፤ በቃሉ ለያዘውና ለሠራበት ይማልዳል እንዲሁም ለነሱ ጀነትን ይለምናልና ነው ::

* ቁርኣን ልብን እንደተመሳሳዮችና ሰሜቶች ካሉ በካይ ነገሮች የሚያጸዳ ፤ ጥራት ይገባውና ወደ ፈጣሪው ታላቁ አላህ የሚያቀርብ ነው ፤ እንዲሁም ዘላቂ የሆነውን ተድላ ለማግኘት ተግቶ እንዲሠራ ይገፋፋል ::

* ከቅዱስ ቁርኣን ማንበብ ሥርኣቶች የሚከተሉት ይካተታሉ ፤

* መጽዳትና ውዱ ማድረግ ::

* ወደ ቂብላ መዞር ::

* በስርኣትና በአክብሮት መቀመጥ ::





* በንባቡ አለመጣደፍ ::

* ፍርሃትን በልብ ማሳደር

* ለወንጀሉና ወሰን ለመተላለፉ ሐዘንን ግልጽ ማድረግ ::

* አላህን በመፍራትና ለቃሉ ታላቅነት ማልቀስ ::

* በንባቡ ድምጽን ማሳመር ::

* የሰጋጆችን ስግደት እንዳያበላሽ በመስጋት ድምጽን ከፍ አለማድረግ ::

* በንባቡ ጊዜ ማሰተንተን ::

* ልብን ማሰባሰብ ::

* የአላህን ታምራት ማሰላሰል ::

* የዚህን መጸሓፍ ደምብ ሰዎች ገቢራዊ ማድረጋቸው በምድር ጥላትን ለመቻልና በሱም

ላይ ድልን ለመቀዳጀት ዋነኛ ምክኒያት መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል ። ሙስሊም ወንዲሜ ሆይ ወደ ጌታህ ለመቃረብ ፍጠን ፤ ይህን መጽሐፍም አጥብቀህ ያዝ ፤ ወደ አላህ ለመቅረብ ማንም ሰው እንዳይቀድምህ በአጽንኦት ሥራ ፤ በአንተ ወደሱ መመለስ አንድ ቤተሰብ መንግድ የወጣ ወገኑ በመመለሱ ከሚኖረው ደስታ የበለጠ አላህ ይደሰታልና ።





# - 4 በመልእክተኞቹ አምናለሁ

በመልእክተኞቹ አምናለሁ ። ታላቁ አላህ ከሰዎች መካከል መልእክተኞችን መርጦ ህግጋቱን እንዲያውቁና ለሰዎችም እንዲያስተምሩ በነሱ ላይ ትንቢት አውርዷል ። ለነሱ የታዘዘ ጀነትን ይውራሳል ፤ በነሱ ላይ ያመፀ ደግሞ ገሀነም ይገባል ።

* ከዚያም እውነተኛነታቸውን በሚጠቁሙና ሀሰት የሚያሉትን ሰዎች ለማሳምን የሚያገዙዋቸውና ጠንካራ መረጃ በሚሆኗቸው ታምራት ደግፏቸዋል ።

* የመልእክተኞች መጀመሪያ ነብዩ ኑሕ ሲሆኑ መደምደሚያቸው ደግሞ ነበዩ ሙሐመድ - ሰ.ዐ.ወ -ናቸው ።

* እነሱም ሰዎች ሲሆኑ እንደማንኛውም ሰው ይበላሉ ፤ ይጠጣሉ ፤ ሚሰት ያገባሉ ፤ ይታመማሉ ፤ ይሞታሉ ። ይሁንጂ እነሱ ከአላህ

ፍጥረታት ምርጦችና ከኃጢያትም የተጠበቁ ናቸው ።

* የአላህ መልእክተኞች በዙዎች ናቸው ።

ከነሱም ታላቁ አላህ በቅዱስ ቁርኣን የሚከተሉትን አውስቷል ፡ ሙሐመድ - ሰ.ዐ.ወ - የእጅግ ርህሩሁ ወዳጅ ኢብራሂም ፤ አላህ ያናገራቸው ሙሣ ፤ የአላህ ቃል ዒሳ ፤ ኑህ ሲሆኑ ። እነዚህ አላህ እዝነትና ደህንነት ያውርድባቸውና ከመልእክተኞች የቁርጠኝነት ባለቤቶች ናቸው ። እንዲሁም ኢስማዔል ፤ ኢስሓቅ ፤ ያዕቆብ ፤ ሃሩን ፤ አዩብ ፤ ዩኑስ ፤ ሱለይማን ፤ ዳውድ ፤ ያሕያ ፤ ዘከርያ ፤ ሁድ ፤ ሷሊሕ ፤ ዩሱፍ ፤ ሹዓይብ ፤ ኢልያስ ፤ ሉጥ ፤ ዙልኪፍል ፤ እድሪስ ። እንዱሁም ሌሎች ብዞዎች ሲኖሩ ከፊላቸው በቅዱስ ቁርኣን ታሪካቸው የተወሳ ከፊላቸው ደግሞ ታሪካቸው ያልተውሳ ናቸው ።

* የአላህ መልእክተኞች የመጀመሪያ ጥሪ ወደ አላህ አንድነት ሲሆን አጥብቀው የከለከሉት ደግሞ በአላህ ማጋራትን ነበር ። አነሱ ሁላቸውም - ለፈጣሪ መገዛት የሚለውን - የእስልምና እምነትና የፈጣሪ አንድነት







ጥሪ ይዘው የመጡ ሲሆን ህግጋታቸው ፤ ጥራት ይገባውና ለታላቁ አላህ አምልኮት ማድረሻ ዘደዎቻቸው የተላያዩ የሆኑት ዘመናታቸውና ቦታዎቻቸው የተላያዩ ከመሆናቸው የተነሳ ብቻ ነው ።

* መልእክተኞችም በነብዩ መሐመድ - ሰ.ዐ.ወ - መምጣት አብስረው በሚላኩባቸው ጊዜ እንዲያምኑባቸው ለተከታዮቻቸው ተእዛዝ እያስተላለፉ ነበር ያለፉት ።

* ከመልእክተኛና ነብይ መካከል ያለው ልዩነት - እንደሚከተለው ይሆናል - መልእክተኛ ማለት ለሰውች እንዲያደርስ አዳድስ ህግጋት የያዘ ትንቢት የወረደለት ነው ። ነብይ ማለት ደግሞ ከሱ በፊት የነበሩ መልእክተኞችን ህግጋት እንዲያስተምር የተላከ ነው ።

* ከመልእክተኞች ከአላህ ዘንድ በላጩ ፣ በነሱ ላይ ሰላም ይሁንና ከኢብራሂም ልጅ ኢስማኢል ዘር የሆኑት መሐመድ - ሰ.ዐ.ወ - ሲሆኑ ለሰው ልጅ ሁሉ የላከቸው ፤ በነብይነታቸው ነብይነቶቸን ፤

በመልእክተኝነታቸው መልእክትኝነቶችን የደመደመባቸው በመሆኑ አምናለሁ ::

* እንዲሁም በታምራት የደገፋቸው ከመልእክተኞች ሁሉ ያበለጣቸው በመሆኑም አምናለሁ :: እንዲሁም መልእክተኝነታቸውን ከመልእክተኝነቶች ሁሉ ፤ ህግጋታቸውን ከህግጋቶች ሁሉ ፤ መጸሐፋቸውን - ቁርኣንን - ከመጸሓፎች ሁሉ ፤ ህዝባቸውን - ሙስሊሞችን - ከሌሎች ህዝቦች ሁሉ አብለጧል ::

* ጌታቸው ከሳቸው በፊት ከነበሩ ነብያት ለአንዱም ያለሰጣቸው ነገሮችን ሰጥቷቸዋል ከነሱም የሚከተሉት ይካተታሉ ፡

1 - አልወሲላ ፤ እሱም አላህ ለነብዩ - ሰ.ዐ.ወ. - ያዘጋጀው በጀነት ውስጥ የሚገኝ ታላቅ ደረጃ ነው ::

2 - አልከውሰር ፤ አሱም ከእጅግ ርህሩሁ ዙፋን ስር የሚፈስ ወንዝ ነው ::

3 - አልሐውድ ፤ አሱም በትንሳኤ ቀን መስሊሞች እንጂ ክሱ ሌላ ሰው የማይጠጣበት ገንዳ ነው ::







በዚያን እለት ሰዎች እጅግ ይጠማሉ ፤ ሁሉም ሰው እንደየሥራው ላባቸው አስከ ጉልበታቸው ፤ አስከ ወገባቸው ፤ አስከ ትከሻቸው ይደርሳል :: ሙስሊሞች -ከዚያ ገንዳ - ነብዩ -ሰ.ዐ.ወ - በተከበሩት እጆቻቸው በሚሰጧቸው ብርጭቆዎች ይጠጣሉ ፤ ከዚያም በኋላ ለዘላለም ጥም የሚባል ነገር አያገኛቸውም ::

4 - ምልጃ ፤ እሱም በትንሳኤ ቀን የሚለገሱት ምስጉኑ ደረጃ ነው :: ነብዩ - ሰ.ዐ.ወ - ከሙስሊሞች ወንጀለኞቹ ከእሳት እንዲወጡ አላህ ዘንድ ይማልዳሉ :: በሷም ከአላህ በስተቀር የሚያመልኩት የለም መሐመድም መልእክተኛው ናቸው ያለ አንድም ሰው አይቀርም :: ከወንጀሉ ከፀዳ በኋላ ይወጣል እንጂ - ምእምን - ወንጀለኛ በእሳት ለዘላለም አይኖርም ::

* በሁሉም ነብያት አምኖ በሙሐመድ - ሰ.ዐ.ወ - ያላመነ ሰው ከእሳት አይወጣም ::

5 - አላህ ለሳቸው ፤ ለጦራቸው ፤ አስከ ትንሳኤ ቀን አሳቸውን ለተከተል ሁሉ የአንድ ወር እርቀት ላይ እያሉ በጠላቶቻቸው ልብ ፍርሃትን በመርጨት ድልን ሰጥቷል :: ይህም ከሳቸው በፊት ለነበረ አንድም ነብይ አልተሰጠም ::

6 - ምድር ለሳቸውና ለሙስሊሞች ሁሉ ንጹህ መስገጃ ሁናላቸዋለች ፤ ከሳቸው በፊት ለነበረ ነብይ እንደዚህ አልተደረገችም ፡፡

7 - አላህ ወደሰው ለጅና ጅን ሁሉ ልኳቸዋል ፤ አያንዳንዱን ነብይ ለህዝቡ ብቻ ነበር የላከው ፡፡

8 - - ነበዩ መሐመድ - ቀብር መጀመሪያ ትሰነጥቅላቸዋለች ፤ የመጀመሪያው አማላጅና ምልጃቸው የመጀመሪያው ተቀባይነት የሚያገኝ ነብይ ናቸው ፡፡ እንዲሁም የመጀመሪያው የጀነት በር አንኳኪ ሲሆኑ የጀነት በር ጠባቂ ሪድዋን ማን ነው ይላቸዋል ፤

ሙሐመድ ነኝ ይሉታል ፤ ለአንተ እንጂ ካንተ በፊት ለሌላ ሰው ላልከፍት ታዝዣለሁ ይላቸዋል ፡፡

እንዲሁም ከነብዩ - ሰ.ዐ.ወ - ታምራት የሚከተሉት ይካተታሉ ፡

* ጨረቃ መንሰንጠቅ ፡፡

* በኡሑድ ጦርነት የውጣውን የቀታዳን ዓይን - በአላህ ፈቃድ - ማስመለሳቸውና ከሌላኛው ዓይኑ የበለጠች ጤናማ መሆኗ ፡፡







* በኡሑድ ጦርነት የተሰበረውን የብንል ሐከም እግር ማዳን ፡፡

* በአንድ ከሀዲ ፊት ዛፉ እንዲመሰክር ጠ ይቀውት ሦስት ጊዜ በመመስከሩ ከሀዲው እስልምናን መቀበሉ ፡፡

* ንግግር ሲያደርጉ ይደገፉት የነበረው ዛፍ ቀንዘል የተውት ጊዜ ማለቀሱና እጃቸውን እስከሚጥሉበት ደረስ ዝም አለማለቱ ፡፡

* እንዲሁም የቀረበላቸውን ምግብ በማብዛት ፤ ሁለት እፍኝ በሚሆን ምግብ ከሰማኒያ በላይ የሚሆኑ ሰዎች እስኪጠግቡ መብላታቸው ፡፡

* እንደዚሁም የሑደይቢያ ቀን ውሃን ማበዛታቸው ፤ በዚያን ቀን በጦሩ ውስጥ አንድ ስህን ውሃ ብቻ ሲቀር ነበያችን - ሰ.ዐ.ወ - እጃቸውን ባስገቡ ጊዜ ውሃ ከጣቶቻቸው መካከል እንደምንጭ ይንዶለዶል ጀመር ፤ አንድ ሺህ አራት መቶ ያህል የነበሩት ሰዎች በሙሉ ጠ ጥተው ለስግደትም ተፀዳጁ ፡፡

* እንደዚሁም ወደሩቁ መስጊድ በሌሊት መጓዛቸው ፤ ወደላይኛቹ ሰማያትና ወደ ሲደረተል ሙንተሃ ማረጋቸው ፡፡

* ከነብዩ - ሰ.ዐ.ወ - ታምራት -አሁንም የሚከተሉት ይካተታሉ - ስላለፉት ህዝቦችና ስለነብያቶቻቸው ማውራታቸው ፤

የማያነቡና የማይጽፉ ያለተማሩ ሁነው ሳለ ፡፡ እንዲሁመ የፋርስና የሩም አገሮች እንደሚከፈቱና ወደሱ የተላከውን የመልእከተኛውን ሰ.ዐ.ወ - ደብዳቤ የቀዳደደው የኪስራ ግዛት እንደሚበጣጠስ ወደፊት የሚሆነውን ነገር መተንበያቸው ፡፡ ሌሎችም ብዙ ታምራቶች አሉ ፡፡

* ከታምራቶቻቸው በጣም ታለቁ ቅዱስ ቁርኣን ነው ፡፡ እሱም እስከትንሳኤ ቀን ዘላቂው ታምር ነው ፡፡

* ከዚያም ጥራት ይገባውና ታለቁ አላህ ስማቸውን ከስሙ ጋር በማቆራኘት ፤ ከአላህ በስተቀር የሚገዙት የለም ሙሐመድ ደግሞ መልእክተኛው ነው በሎ መመስከር ማንኛውም





ባሪያ ወደ እስለምና የሚገባበት የመጀመሪያ ቃል አንድሁም ከዚህች ዓለም ሲወጣ የመጨራሻው ሊሆን የሚገባው ቃል በማድረግ መወሳታቸውን ከፍ አድርጓል ፡፡ የመጨራሻ ቃሉ ከአላህ በስተቀር የሚገዙት የለም የሚለው ቃል የሆነለት ሰው ጀነትን ይገባል ፡፡

* በመሆኑም በእኛ ላይ ከነብያችን -ሰ.ዐ.ወ - ሀዲስ - ቃል - የማነንም ቃል እንዲሁም ከትእዛዛቸው የማንኛውንም አዛዥ አስተያየት ያለማስቀደም ግዴታ አለብን ፡፡ ወገኔ ሆይ ሰዎች ወደነብያችን በመጓዝ ቢቀድሙህም እንኳ ፤ በነገሮችህ ሁሉ ወደ ፈለጋቸው ተጓዝ ፤ ከሱ ሌላንም አትከተል ፡፡ ሁላችንም በትእዛዛቸው ዙሪያ መሰባሰብ ፤ እናም ለመልእከተኛው የታዘዘ ለአላህ እንደታዘዘ ነውና ለትእዛዛቸው መገዛት ይኖርብናል ፡፡

* የአላህ መልእክተኛ በሚለው ስማቸው ብቻ እንጂ ፤ ሙሐመድ ብቻ በማለት ላንጠራቸው ይገባል ፡፡

* ሥነ ስርአታችን ስርአታቸው ሊሆን ፤ እናም በአተኛኘታቸው ፤ አመጋገባቸው ፤ አካሄዳቸው ፤ አሰጋገዳቸው ፤ በጾማቸው ፤ በምጽዋት አሰጣጣቸውና በሃማኖት ትግላቸው እንዲሁም በአጠቃላይ ሁኔታቸው ልንከተላቸው ይገባል ::

* ከራሳችን ፤ ከልጆቻችን ፤ ከወላጆቻችንና ከሰዎችም ሁሉ አብለጠን ልንወዳቸው ግዴታ አለብን ::

* የአላህ መልእክተኛን - ሰ.ዐ.ወ - የሚወድንና የሚከተልን የመውደድ ፤ የሚጠላቸውንና ህግጋታቸውን የማያከብርን የመጥላት ግዴታ አለብን ::

* አንድ ሙስሊም መእምናን የመውደድ ፤ የመርዳት ፤ እነሱን የመምሰል ፤ ለጉዳዮቻቸው ትኩረት የመስጠት ፤ በመልካም ሥራቸው የማገዝና ከነሱም ወዳጆች የመያዝ ግዴታ አለበት ::

* እንዲሁም ከሃዲዎችና ክህደታቸውን የመጥላት ፤ ለነሱ በመታዘዝ ፤ ጸረ ሙስሊም በመሆን ከነሱ





ጋር ቃል ኪዳን ያለመጋባት ፤ በከንቱ ሥራቸው ያለማገዝ ፤ በባእላቸው ያለመሳተፍ ግዴታ አለበት :: ይሁንጂ እነሱን መበደሉ በሱ ላይ እርም ነው ፤ እናም ከነሱ ጋር ሲዋዋል ፍትሃዊ የመሆን ግዴታ አለበት ::

* የነብዩ - ሰ.ዐ.ወ - ባለቤቶች የሁኑትን የምእምናን እናቶችንና ከነበዮች በኋላ ከሰዎች ሁሉ የበለጡ የሆኑትን የነብዩን ሰ.ዐ.ወ - ባልደረቦች የመውደድ ግዴታ አለብን ::

* እዲሁም ፈለጋቸውን ሕያው ፤ ህጋቸውን ይፋ የማድርግ ፤ ጥሪያቸውን ለሰው ሁሉ የማድረስ ፤ ይህን ስናደርግ ለሚደርስብን ስቃይ « ይህ ደግሞ አይቀሬ ነውና » የመታገስ ግዴታ አለብን ::

* ምክኒያቱም አላህ በፍጥረቱ ደንግጎ ያሳለፈው ወሳኔ ፤ ከነብያት እንዲሁም ከአላህ ተመኪ አንዱም ለዚህ እውነት ጥሪ አድርጎ ያልተጠላና ያልተሰቃየ የሌለ መሆኑን ያመለክታልና ነው ::

* አንተ ሙስሊም ሆይ ተጠንቀቅ ፤ ከሃዲዎች ባንተ ላይ ስቃይ ማድረሳቸው ከእምነትህ ፈቀቅ

እንዳያደርግህ ። የአላህ መልእክተኛ - ሰ.ዐ.ወ - ባልደረቦቻቸው ጥቂት በነበሩበት ጊዜ ስቃይ ደርሶባቸዋል ፤

ባልደረቦችም ስቃይ ደርሶባቸው ታግሰዋል ።

* ሰዎች አይምሮው የተነካ ፤ ደረቅና ኋላ ቀር የሚል ቅጽል ሳንተ መስተታቸው ፤ ጭንቅላቱ የታጠበ ማለታቸው ፤ ቁርጠኝነትህን እንዳያዳከመው ። - ወደ ኋላ መለስ ብለህ ብትመለከት - በአላህ መልእክተኛ - ሰ.ዐ.ወ - መልካም አርኣያነትን ታገኛለህ ፤ ባለ ሥነ ግጥም ወይም እብድ ነው ተበለዋል ።፤

* መስመር የሳተ አጥናፍ እደርሳለሁ ባይ አክራሪ መባልህ አይጎዳህም ። ይህ ከምእምናን አንፃር ያለቸው የካህዲዎች የዘወትር አመል ነው ።

﴿وَإِذَا رَأَوْهُمْ قَالُوٓا۟ إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ لَضَآلُّونَ﴾ [ المطففين:٣٢].

« ባዩዋቸውም ጊዜ እነዚህ በርግጥ ተሳሳቾች ናቸው ይሉ ነበር » - ምዕራፍ ኢለሙጠፊፊን 32 -







* ሰዎች ወደ ሁለት በሚከፈሉበት ጊዜ ነብይህ ሙሐመድ -ሰ.ዐ.ወ - ካሉበት ቡድን መሆንህ አይበቃህምን ?

* በደለኛ ጣቶቹን እየነከሰ ወይኔ ምነው በመልእክተኛው መንገድ ገብቸ በሆን ለሚልበት ቀን ተዋቸው ።

﴿يَوْمَ يَعَضُّ ٱلظَّالِمُ عَلَىٰ يَدَيْهِ يَقُولُ يَٰلَيْتَنِى ٱتَّخَذْتُ مَعَ ٱلرَّسُولِ سَبِيلًا﴾

[الفرقان:٢٧].

* አሸባሪ ወይም ተንኮለኛ በሚሉህ ጊዜ ነገሮች አይምታቱብህ ። ይህ እጅግ በደለኞች በዚህች ዓለምና በመጭዋም ዓለም በምእምናን ላይ የሚሰነዝሩት ከንቱ ወሬ ነው ። በዚያ በትንሳኤ ቀን መላእክት በፊተቸው ደፍተው ወደ ገሀነም ሲጎትቷቸውና ገሀነምን በተመለከቱ ጊዜ

﴿وَقَالُوا۟ مَا لَنَا لَا نَرَىٰ رِجَالًا كُنَّا نَعُدُّهُم مِّنَ ٱلْأَشْرَارِ﴾ [ ص:٦٢].

« ይላሉ ለኛ ምን አለን ? ከመጥፎዎች እንቆጥራቸው የነበሩትን ሰዎች እዚህ አናይምሳ ። » - ምዕራፍ ሷድ 62 -

* ያኔ ምእምናን - መጥፎዎች በለው የሰየሟቸውን በደለኞች - በገነት ከፍተኛ ቦታ ላይ ሁነው ይጠሯቸውና

﴿أَن قَدْ وَجَدْنَا مَا وَعَدَنَا رَبُّنَا حَقًّا﴾ [الأعراف:٤٤].

« ጌታችን ቃል የገባልንን እውነት ሆኖ አገን » ይሏቸዋል ።







# 5 - በመጨረሻው ቀን ማን

በመጨረሻው ቀን አምናለሁ ፤ እሱም የሥራ አገር የሆነችው ይህች ዓለም ጠፍታ የምንዳ አገር የሆነው ቀጣዩ ዓለም ይመጣና መልካም ሥራዎች ጀነት የሚያወርሱበት ፤ መጥፎ ሥራዎች ደግሞ ገሀነም የሚያወርዱበት ቀን ነው ።

* በዚያ የትንሳኤ ቀን ሚዛን ይቆምና እያንዳንዱ ባሪያ የራሱ የሆነን መጽሐፍ ይሰጣል ። መጽሐፉን በቀኝ እጁ የተቀበለ ከነብዮች ጋር ጀነት ይገባል ፤ መጸሐፉን በእግራ እጁ የተቀበለ ደግሞ ከነፊርዓውን - አላህ ከእዝነቱ ያርቀውና - ጋር ገሀነም ይወርዳል ።

* በዚያን ቀን ሲራጥ - ከጸጉር የቀጠነው መተላለፊያ - ይተከላል ያለ ምንም ችግር ለማለፍ የቻለ በቀጥታ ወደ ጀነት ይደረሳል ፤ በመጥፎ ሥራዎቹ ምክኒያት የመተላለፊያው መንጠቆዎች የጠለፉት ወደ ገሀነም ተምዘግዝጎ ይወድቃል ።

* የትንሳኤ ቀን መቃረቡን የሚጠቁሙ ትንንሽና ተላላቅ ምልክቶች አሉ ።

* ታማኝነት መጥፋት ፤ ግድያ መብዛት ፤ ኃይልን ተለግሰው ምግባረ ብልሹዎች በትረስልጣን

* በትንሳኤ ቀን ቅንጣት ታህልም ብትሆን ማንኛውም ሰው መልካምም ሆነት መጥፎ ሥራውን በመጽሐፉ ያገኛታል ::

* በመሆኑም ምእምናን ሆይ ፤ ከአላህ በስተቀር ማነም ሰው በማያውቀው ጊዜና ሣዓት ባሪያው በመሞቱ የመልካም ሥራ መመዝገቢያ ጊዜ ከማለፉ በፊት ለመለካም ሥራ ታታሪ ሁኑ ::

* አንድ ሰው ያ ጊዜው ደርሶ ከሞተ በኋላ ቤተሰቦቹ ያጥቡታል ፤ ይገንዙታል ፤ ይሰግዱበታል ፤ ይቀብሩታል ፤ ከዚያም ነኪርና ሙንከር የተባሉት ሁለቱ መልኣኮች ይመጡና እንዲቀመጥ ካደረጉት በኋላ ማነው ጌታህ ? ምንድን ነው ሃማኖትህ ? ማነው መልእክተኛህ ? በማለት ይጤቁታል ::

* ጌታየ አላህ ነው ፤ ሃይማኖቴ እስልምና ነው ፤ መልእከተኛዬ ደግሞ ነብዩ መሐመድ - ሰ . ዐ . ወ - ነው ፤ - በማለት እንዲመልስ አላህ ከመራው - በመቃብሩ እያለ ወደ ጀነት መመልከት የሚያስችል ቀዳዳ ይከፈትለትና በዚያ ያለውን መኖሪያውን ፤ ህንፃውንና ግዛቱን ያይና በደስታ ይዋጣል ፤ መቃብሩም የዓይን መድረሻ አድማስን ያህል ይሰፋለታል ::



እኔ ሙስሊም ነኝ

መጨበጥ ፤ ሞኞች ስለ አንገብጋቢ ጉዳዮች ሲናገሩ መደመጥ :: ክትንንሽ ምልክቶች ይመደባሉ ::

* የማህዲይ መምጣት ፤ ከትንሳኤ ቀን በፊት የነብዮችን ፈለግ መሰረት ያደረገ መልካም አስተዳደር እንደገና መስፈን ፤ የመሲሕ አደጃል መታየት ፤ ከተላላቅ ምልክቶች ይመደባሉ ::

* ሰላም በሳቸው ላይ ይሁንና ነብዩ ዒሣ ወርደው ሙስሊሞችን በመምራት ከሀዲዎችን መዋጋታቸው ፤

መስቀልን መሰባበራቸው ፤ አሳማን መግደላቸው ፤ ያለ እስልምና ሌላን የማይቀበሉ መሆናቸው እንደዚሁ ከተላላቆቹ ይመደባል ::

* ያንጊዜ በዚህች ዓለም የጭቃም ሆን የማቅ ቤት ነዋሪ ፤ በተከባሪዎች ክብርም ሆነ በተዋራጆች ውርደት አላህ በዚህ ሃይማኖት ያስገባው ከመሆን አያልፍም ::

* ያእጁጅና ማእጁጅ እንዲሁም ሰው የምታናግረው ላም ይከሰታሉ ፤ ጸሐይ በመግቢያዋ ትወጣለች ፤ ቅዱስ ቁርአንም ይነሳል ፤ ሌሎችም ተላላቅ ምልክቶች ይከሰታሉ ::

# እኔ ሙስሊም ነኝ

* ከከሀዲዎች ከሆነ ደግሞ ምንም ዓይነት መልስ መስጠት አይችልም ። በዚያን ግዜ መልስ መስጠ ት የሚቻለው በብልጠትና በአይምሮ ንቃት አይደለምና ።
* ነገር ግን ታላቁ አላህ በዚያች እለት ፣ እሱን ብቸኛ በማድርግ፣ እንደ ግዴታ መወጣት ፤ ለሃይማኖት መዋጋት ፤ ደግ ሥራ ፤ በመልካም ማዘዝ ፤ ከመጥፎ መከልከል ፤ ምጽዋት መስጠት ፤ ቅዱስ ቁርኣን ማንበብ ፤ በከፍተኛ ሙቀት ቀን ያምና በብርድ ጊዜ በሌሊት ለረዥም ጊዜ መቆም ያሉ መልካም ሥራዎችን በዚህች ዓለም ለፈፀሙ ምእምናን ያን ትክክለኛ መልስ ያለ መንገዳገድ እንዲሰጡ ይመራቸዋል ።
* ከከሀዲዎች የሆነ እንደሆነ ደግሞ የአንደኛው ጎን አጥንጡ ከሌላው እስከሚተላለፍ ድረስ መቃብሩ ጥቦ ያጣብቀዋል ፤ በመጥፎ ሥራውም መቃብሩ የገሀነም ጉድጓድ ይሆንበታል ።
* ሙስሊም ወንድሜ ሆይ ለመልካም ሥራ ታታሪ ሁን ፣ ዛሬ ሥራ እንጂ ሂሳብ የለም ፤ ነገ ደግሞ ሂሳብ እንጂ ሥራ አይኖርምና ።
* በዚያን ቀን ታዛዥ የሆኑትና የተገዙት ሙስሊሞች ብቻ ጀነት ይገባሉ ።፤ ታላቁ አላህ በዚያን ቀን እስልምናን እንጂ አይቀበልምና ።





# እኔ ሙስሊም ነኝ

* በጀነት በጆሮ ያልተሰማ ፤ በዓይን ያልታየና በሰው ልብ ያልታሰበ ተድላ ተዘጋጅቷል ። ይህም ተድላ የማያቋርጥ ለዘላለም የሚዘልቅ ነው ፤ የጀነት ነዋሪዎች አይሞቱም ፤ በዚያን ጊዜ ካለው ተድላ እጅግ ታላቁ የዓለማት ጌታ የሆነውን ታላቁ አላህን ማየት ነው ።
* አመጸኞች ፤ ኃጢያተኞች እንደዚሁም ከሀዲዎች ገሀነም ይገባሉ ። በገሀነም አላህ ለከሀዲዎች የማይቋቋሙት ቅጣት አዘጋጅቷል ፤ እነሱም በዚያ የተንሰራፉ ተላላቅ ተራራዎች ሊቋቋሙት በማይችሉት ቅጣት ያለማቋረጥ ይወሰቃያሉ ።
* እዚያ ገሀነም ውስጥ የጣያታት አምላኪዎች በነዚያ ባጠመሟቸው አለቆቻች ላይ ስቃዩ እጥፍ እንዲሆንባችው ይጠይቃሉ ፤

አላህም የሁላቸውም ስቃይ እጥፍ እንዲሆን ያዛል ።
* በመሆኑም ሙስሊም ወንድሜ ሆይ ይህን እውነተኛ እምነት አጥብቀህ ያዝ ፤ በዚህ እምነት አንፃር የቆሙ ሰዎች መብዛት እንዳያታልልህ ። ምክኒያቱም በምድር ላይ ካሉ ሰዎች ለብዞዎቹ ተገዢ ከሆንክ ከአላህ መንገድ ያሳስቱሃልና ። እናም ወደ አላህ መንገድ ከገቡት ጋር ወደ አላህ መንገድ ግባ ።

* ይህውም ከነብዩ መሐመድ ህዝቦች መካከል ፣ ተፃራሪም ሆነ ውርደት ሊያጎናጽፈው የሚሞክር ተጻእኖ ሊያሳድርበት የማይችል ሆኖ እስከ ትንሳኤ ቀን ለእውነት በይፋ የሚቆም አንድ ቡድን አይጠፋምና ::

* እዚያ ደረጃ ለመድረስና ከዚያም ዓይመቱ አዘቅጥ ለመውጣት ብልሃቱ ምን ይሆን ? ወደ እስልምና ቀዳሚና ወደ አላህ ቀራቢዎች ለመድረስ ፤ እንዲሁም ደግሞ ከችልተኞቹና ከጠፊዎቹ ለመራቅ ጥበቡ ምን ይህን ? ብልሃቱ ያለፈውን ስህተት የሚያርም እውነተኛ መጸጸትና ከእድሜ የቀረውን የሚያበጅ ምግባረ ስናይ ፤ እንዲሁም ቅኑን መንገድ መከተልና ከሱም ላለማጋደል ቁርጠኛ መሆን ነው ::

* ስትገዛ ፤ ስትሸጥ ፤ ስታገባና መሬትን ስታቀና አላህ በፈቀደልህ ሁኔታ በአካልህ ከሰዎች ጋር ተዋዋል ::

* በዚህች ዓለም ባለ በማንኛውም ነገር ልብህ አይንጠልጠል ፤ ባንፃሩም ልብህን መሆን ወደሚገባበት ወደ ታላቁ አለህ ዙፋን ስር ምራው ፤ በዚያም እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ አንዴም ቀና ያለማለት እንደሰገደ እንዲዘልቅ አድርገው ::





# 6 -በፍርድና ውሳኔው አምናለሁ

* እሱም አላህ በፍጥረታት ውስጥ ያለውን ሁሉ ፤ እስካሁን የሆነውን ፤ እስከ ትንሳኤ ቀንም ወደፊት የሚሆነውን ያውቃል ፤ የቅንጣት ሁኔታም እንኳ ከእውቀቱ ውጭ አይሆንም ፤ እሱ ሳይፈጥራቸው በፊት የባሮቹን ሥራ ፤ ሲሳያቸውን ፤ እድሚያቸውን ፤ ከነሱም የትኞቹ የጀነት የትኞቹ ደግሞ የገሀነም መሆናቸወን አውቋል ብለን ማመናችን ነው :፤

* አላህ እነዚህን ውሳኔዎች መሬትና ሰማያት ከመፈጠራቸው ከ50 ሺህ ዓመታት በፊት በተጠበቀው ሰሌዳ መዝግቧቸዋል :: የዚህን የተጠበቀ ሰሌዳ ምስጢር ወደ አላህ የሚቀርብ መልአክም ሁነ የሱ መልእክተኛ የሆነ ነብይ ሊያውቀው ከቶ አይችልም ::

* አንድ ሽል በናቱ ሆድ በሚጠነሰስበት ጊዜ ታላቁ አላህ ፣ ወንድ ወይም ሴት መሆኑን ፤ የሚሳዩን መጠን ፤ የሥራውን ዓይነት ፤ እድሜውን መመለሻውን - ወደ ጀነት ወይስ ወደ ገሀነም - መጥፎም ሆነ ደግ የሚያጋጥመውን ነገር ሁሉ መልአኮች እንዲመዘግቡ ያዛል ::

* የመወሰኛይቱ ሌሊት ጊዜ የሰዎች እድሜ ፤ ሲሳያቸው ፤ በዚህ ዓመት የሐጅ ሥራ የሚያደርሱት እነማን ናቸው የሚሉትና ሌሎችም ነገሮች የተካተቱበት የዓመቱ ውሳኔዎች ይወርዳሉ ፤ የዚያ ዓመት ተግባራት በሙሉ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል ።

* ከዚያም ውሳኔዎች በየጊዚያቸው ወደየሰዎቻቸው ይወርዳሉ ፤ አላህም ሰዎችን ከፍ ሌሎችን ደግሞ ዝቅ ያደርጋል ።

* የአላህ ፈቃድ ተፈጻሚ በመሆኑም እናምናለን ፤ የፈቀደው ይሆናል ያልፈቀደው ደግሞ አይሆንም ፡፤

አላህን የሚያሸንፈው ነገር የለም ፤ እሱም ልቦችን ቀለባባሽ ነው ። በችሮታውና በእዝነቱ ለፈለገው ቅኑን መንገድ ይመራል ፤ በብልሃቱና በፍትሃዊነቱ ደግሞ የፈለገውን ከቅኑ መንገድ እንዲያጋድል ያደርገዋል ። ቅኑን መንገድ ማወቅ ያለበትን እንዲሁም ከቅኑ መንገድ ማጋደል የሚገባውን ተመልካቹ እሱ ብቻ ነው ።

* አላህ ስለሚሠራው ነገር አይጠየቅም ፤ ሰዎች ግን ይጠየቃሉ ።





አላህ ሁሉን ነገር የፈጠረ በመሆኑም እናምናለን ። በዓለም ውስጥ የምትገኝ ቅንጣት ሁሉ አላህ አካሏን ፤ ፀጥታዋንና እንቅስቃሴዋን የፈጠረው እንጂ አይደለችም ።

* ባሮቹን እንደዚሁም ሥራቸውን የፈጠረ ፤ እንዲሁም እሱ ሰዎች ሥራቸውን እንዲመርጡ ችሎታና ፍላጎት የፈጠረላቸው በመሆኑም እናምናለን ።

* እንዲሁም ታላቁ አላህ ፍጥረታት ሁሉ እንዲገዙለት ያዘዘና ፣ ይህንም ካደረጉ ጀነት እንደሚያስገባቸው ቃል በመስጠቱ ፤ ባንፃሩም እንዳያምጡ ያሰጠነቀቃቸው ያን ካደረጉ ግን ገሀነም እንደሚያስገባቸው ያጠነቀቀ በመሆኑና ከሥራዎች የሚችሉትን እንጂ ያላስገደደ በመሆኑ እናምናለን ። እንዲሁም ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ በምርጫቸው ፤ በፍላታቸውና በችሎታቸው ምእምናንና ከሀዲዎች ሁነው ወደ ሁለት የተከፈሉ በመሆኑም እናምናለን ። ይህን ሁሉ ታላቁ አላህ በነሱ ላይ ፈጥሮታል ።

* የመልካም ሥራ ምንዳም ሆነ የመጥፎ ሥራ ቅጣት የእምነትን ህግጋቶች ከመከተል ጋር የተያያዙ እነጂ ከዚያ በፊት አላህ በእውቀቱ ቀድሞ የፈረደባቸው ውሳኔ አይደለም ፤ እንዲሁም

ቅንጣት ታክል መልካም የሠራ ምንዳ የሚያገኝባት ፤ ቅንጣት ታክልም ተንኮል የሠራ ደግሞ የሚቀጣበት በመሆኑም እናምናለን ::

* ማንኛውም ነገር ቋሚ ህልውናውን የሚያገኘው በሚቋጭበት ሁኔታ በመሆኑና ማንኛውም ባሪያ በጀነት መደሰትንም ሆነ በገሀነም መሰቃየትን የሚያስከትል ሥራን ለማከናወን ሁሉም ለተፈጠረለት ጥርጊያ መንገድ የተቀየሰለት በመሆኑም እናምናለን ::

* በመሆኑም ማንኛውም ባሪያ መቋጫው እንዳይበላሽበት መስጋት ፤ ታላቁ አላህ ቅኑን መንገድ እንዲመራው መለመንና መጸለይ ፤ ለመገዛቱ እንዲያበረታው ፈጣሪን ዘወትር መጠየቅና ከማመጸም እዲያርቀው በሱ መጠበቅ ይኖርበታል :: ይህውም በአላህ ኃይል ካልሆነ በስተቀር ይህን ሁሉ ለመፈጸም ማንኛውም ባሪያ ብልሃትም ሆነ ችሎታ የለውምና ::

* ምእምናን ደግም ይሁን ክፍ ፤ በጭንቅም ቀን ይሁን በደስታ ጊዜ የሚከሰተውን የአላህ ፍርድና ውሳኔ በደስታ ይቀበላሉ :: እንዲሁም በአላህ ፍርድ ካልሆነ በስተቀር ማንም ሰው ሊጠቅማቸው ፤ ደግሞም አላህ በደነገገው ነገር ካልሆነ በስተቀር





ማነም ሰው ሊጎዳቸው የማይችል በመሆኑ እርግጠኞች ናቸው ::

* አንድ ባሪያ ከዚያ ከደረሰበት ነገር የሚያመልጥ ሊሆን ፤ እንዲሁም ያ የሳተው ነገር የሚያገኘው ሊሆን የማይችል በመሆኑ እርግጠኛ እስካልሆነ ድረስ የእምነትን ጣፋጭ ጣዕም ሊያገኝ ከቶ አይችልም ::

* በመጨረሻም አላህን አመሰግናለሁ ፤ እኔንና ሌሎች ሙስሊሞችን ጀነት እንዲያሰገባን ፤ እንዲሁም እኔንና ሌሎች ሙስሊሞችን ከአሳት እንዲጠብቀን እጸልየዋለሁ ኣሜን ::

ታላቁ አላህ በነብ ሙሐመድ - ሰ.ዐ.ወ - በቤተሰቦቻቸውና እንዲሁም በባለደረቦቻቸው አዝነትና ሰላም ያውርድ ::

የመጨረሻ ጸሎታችን የዓለማቱ ጌታ ለሆነው አላህ ምስጋና ይገባው የሚለው ቃል ይሆናል ::

بسم الله الرحمن الرحيم

﴿ وَمَن يَبۡتَغِ غَيۡرَ ٱلۡإِسۡلَٰمِ دِينٗا فَلَن يُقۡبَلَ مِنۡهُ وَهُوَ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ﴾

[آل عمران:٨٥]

**للمساعدة في التوزيع الخيري اتصل على ٠٠٢٠١٠١٤٥٩٦١٣**

**للاقتراحات اتصل على البريد الإلكتروني anamuslim@windowslive.com**

**WWW.Iam-Muslim.com**

دار الخلفاء الراشدين

**١٤٣١ هـ - ٢٠١٠ م**

جميع الحقوق مكفولة لكل مسلم ومسلمة

**رقم الإيداع: ٢٠٠٩/٢٢٢٧٤**

**الإدارة : ٠١٠٥٠١٣١٥١ المبيعات: ٠١٢٠١٥٢٩٠٨**



**كتاب لا غنى عنه لكل مسلم ومسلمة**

# أنا مسلم

**باللغة الأمهرية**

محمد أشرف صلاح

توزيع

دار الخلفاء الراشدين
الإسكندرية - أبو سليمان - ش عمر
أمام مسجد الخلفاء الراشدين
٠١٠٦٧١٤٧٦٨

دار الفتح الإسلامي
الإسكندرية - مصطفى كامل
بجوار مسجد الفتح الإسلامي
٠١٢٥٨٣٤٥٧٤